
# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1-10/2019 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበራቸዉ፡፡ በዚሁ መሰረት አብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ ዝናብ ማግኘታቸዉን ቀጥሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በምስራቅ ትግራይ፣ በምስራቅ አማራ፣ በመካከለኛዉ እና ምዕራብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ አፋር፣ በጥቂት በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ የመካከለኛዉ እና ምዕራብ ኦሮሚያ እንዲሁም ምስራቅ አማራ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በሲሪንቃ 53.1፣ በኮምቦልቻ 52.7፣ በወላይታ ሶዶ 49.1፣ በመተሃራ 46.6 እና 40.5፣ በኩሉምሳ 41.9፣ በጋቲራ 38.0፣ በአርጆ 34.2 እና በአዳማ 30.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ከፊል ደመናማ ሆነዉ ሰንብተዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በደቡብ ትግራይ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ክልል 3 ና 4፣ በምዕራብ እና ምስረቅ ሸዋ፣ በቄለም ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ እና በጅማ ዞኖች ላይ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የደበቡ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ ከ25-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-8 ለሚደርሱ ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአሶሳ ዞን፣ በጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ፣ በባሌ፣ በምዕራብ አርሲ፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በአፋር ክልል ዞን 05 እና 03 እንዲሁም በአሶሳ ዞን ላይ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4 ቀናት በታች ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር የደቡብ ትግራይ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ክልል 3 ና 4፣ አዲስ አበባ፣ የቄለም ወለጋ፣ የኢሉአባቦራ እና የጅማ ዞኖች፣ የምዕራብ እና ምስረቅ ሸዋ፣ የአፋር ክልል ዞን 03፣ የአሶሳ ዞን፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀድያ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ጋሞጎፋ፣ ሲዳማ እና ጌዴኦ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ1    ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2  እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1- 0/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ

# በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት የኤፕሪል የመጀመሪያው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸዉ የተተነተኑ የአግሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገታቸው ላይ የጎላ ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን፤ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በጎ ጎን ነበራቸው፡፡ በአንፃሩም በአንዳንድ የመካከለኛዉ እና ምዕራብ ኦሮሚያ እንዲሁም ምስራቅ አማራ አካባቢዎች የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በጥቂት ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ቢኖረውም፤ ለአብዛኛው የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ የጎላ አስተዋፅኦ ነበረው ፡፡ በሌላ በኩል በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ ያነሰ አነስተኛ ዝናብ ከነበረው ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ጋር ተዳምሮ በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እና የሰብሎች ዉሃ ፍላጎት ማሟላት ላይ መጠነኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 4)።


ካርታ 4    እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 10/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>ውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች የላይኛዉ ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ሽምጥሽለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛዉና የታችኛው አዋሽና አባይ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው የላይኛዉ ገናሌዳዋ፣ መካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ስምጥሸለቆ፣ የባሮኮቦ ምስራቃዊ ክፍል፣ የላይኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ እንዲሁም ጥቂት የመካከለኛውና የላይኛው ተከዜ አዋሳኝ ኪስ ቦታዎች ሲሆኑ፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏለል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5፡ እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 10/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ
የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20/2019 የሚኖረው
# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከቀዳሚው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው። በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ።

በመጪው ኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተለይም በበልግ ዝናብ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ ከሶማሌ ክልል ሰሜናዊ ክፍል ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች እንዲሁም የአፋር ዞን 1፣3 እና 5 መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከሚኖሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል። በተጨማሪም የምሥራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ጋምቤላ፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች እንዲሁም የደቡብ ሶማሌ ዞኖች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛዉ አስር ቀን ከእርሻ እንቅስቃሴ አኳያ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች በስርጭትም ሆነ በመጠን ረገድ ጥሩ ዝናብ የሚያገኙበት እንዲሁም የመኸር ወቅት የረጅም ጊዜ ሰብል አብቃዮች የማሳ ዝግጅትና የዘር እርሻ እንቅስቃሴ የሚጀምሩበትና ዋነኛ

የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ዝናብ የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ እርጥበት ሊቀጥል እንደሚችልና በተለይም በበልግ ዝናብ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የበልግ ሰብሎች ጠቀሜታ ሲኖረው ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲሁም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለማቆርና ለማጠራቀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ስለሚጠበቅ አርሶ አደሮችም ሆኑ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አስፈላጊውን ዝግጅት ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ የሚጠበቀው ከመደበኛው በላይ የሆነ የእርጥበት መጠን በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረዉ ቢችልም፣ በቀጣይነት ለሚኖረው ለአዝዕርቱም ሆነ ለግጦሽ ሳር የውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ሰለሚኖረው የተለያዩ የውሃ ማቆር ስራዎችን በማከናወን ዕጥረት በሚገጥምበት ጊዜ በአንዳንድ ማሣዎች ላይ ዉሃዉን ለመጠቀም ይረዳል።

## <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ከባለፉት አስር ቀናት የተሻለ የዝናብ ስርጭትና መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል። በዚህ መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ስምጥሸለቆ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ተከዜ፣ በጥቂት የላይኛው አዋሳኝ አፋርደናክል፣ በላይኛውና በታችኛዉ አዋሽ፣ በላይኛውና በመካከለኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም በገናሌዳዋ የላይኛዉና የደቡበዊው ክፍል አዋሰኝ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው የተሻለ የእርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተ□ማሪም በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተተነበየ በመሆኑ ይህ ሁኔታ ወራጅ ውሃ እንዲኖር አስተዋፆ ስለሚያደረግ ለውሃ ሃብት ግብኣት ጥሩ አሰተዋፅዖ ይኖረዋል። በተጨማሪ በጥቂት ታችኛዉና በመካከለኛው አባይ እንዲሁም በላይኛዉ ኡጋዴን አዋሰኝ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ የተቀሩት ተፋሰሶች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል።